# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 5 ቁጥር 4 ሐምሌ 21 ቀን 2013 ዓ.ም.

## <u>ጦርነቱ?</u>

ሀገራችን ኢትዮጵያ በተለያየ ዘመን አስቸጋሪ እና ፈታኝ ወቅቶች ቢገጥሟትም የሕዝቧ የሀገር እና ሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ሉዓላዊነቷን ሊያስነካ፣ አንድነቷን ሊያናጋ አልቻለም። ድህነትና ችግር የቤተሰቡ አካል የሆነው ሕዝባችን በተፈራረቁበት ራስ ወዳድና አምባገነን አገዛዞች ቢማረርም ሀገር ሲባል ግን ቂሙን አራግፎ፣ ድህነቱን እረስቶ፣ “ማን እንደ ሀገር” ብሎ ትውልድ እየተቀባበለ ኢትዮጵያችን ዛሬ አለችበት ፈታኝ ወቅት ላይ ደርሳለች። ለጦርነት የሚዳርጉን ታዲያ ሁሌም ለእኛ የማይተኙ ባእዳን ኃይሎች በአንድ በኩል ሲሆኑ  የአገዛዞች አትንኩኝ ባይነት፣ ሥልጣን ወዳድነት፣ አፍኖ በመግዛት፣ ሁሉን ነገር የሚፈታ ሕዝባዊ መንግሥት እንዳይፈጠር የሚፈጥሩት ብልሹ ሥርዓት እራሱ የእርስ በእርስ ግጭቶችንና ትግሎችን በሌላ በኩል ወልዷል። ኢትዮጵያን በተዘዋዋሪ መንገድ ለማዘዝ፣ የራሳቸውን አጎብዳጅ አገዛዝና መሪ ለማስቀመጥ፣ ካልሆነም በሌሎች ላይ ያደረጉትን ሀገርና ሕዝብ መበታተን ዛሬም በሀገራችን ለመተግበር የማይፈነቅሉት ድንጋይ፣ የማያውጠነጥኑት ሤራ፣ የማይሸርቡት ተንኮል እንደሌለ ልንገነዘብ ይገባናል።

ጦርነት አውዳሚ ነው። ጦርነት የሀገርን ኢኮኖሚ ይጎዳል። ጦርነት ሳንወድ በግድ ሕይወት ያስከፍላል። ወቅት እየጠበቀ በሚከሰት ጦርነት ከሚባክነው ሀብትና ንብረት፣ ከሚጠፋው የሰው ሕይወት፣ ጥሎ ከሚያልፈው ጠባሳ ለማገገም ዓመታት ይቆጠራሉ። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያችን የህልውና አደጋ ላይ ነች። ኢትዮጵያ ተበታትና እርስ በእርስ ግጭት ውስጥ ትዘፈቅ ዘንድ የመጨረሻው መጀመሪያ እያንዣበበ ነው። የመንግስት ችግር እንደተጠበቀ የሀገራችንን እልውና ማስጠበቅ፣ አለመበታተናችንን መዋጋት፣ ይኖርብናል። ኢትዮጵያ በአለፉት ሦስት ዓመታት ያስመዘገበችው የሰው ልጅ እልቂት ቀላል አይደለም። የለውጥ አራማጁና አሸጋጋሪው የጠ/ሚር ዶክተር ዐቢይ አገዛዝ ሆ! ተብሎ የተጮኸለትን ያህል ዝም ማሰኘት ብቻ ሳይሆን ሀገራችንን እጅግ ግራ አጋብቷል። የሻሸመኔ፣ የቤኒሻንጉል፣ መተከል፣ የሱማሌ፣ የደቡብ፣ የአጣዬ እና የሌሎች በርካታ አካባቢ እልቂቶችና ፍጅቶች አገዛዙ ላይ ጥርጣሬ ከመጫር አልፎ ተቃውሞን አስነስቷል። በየአካባቢው በተደረገ ጭፍጨፋ በተለይ አማራው ላይ ማነጣጠሩ የማይካድ ሀቅ ነው። በንብረት ውድመትም የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን ከፍተኛውን ድርሻ ትይዛለች። ይህ ሂደት በተለያየ እትሞቻችን በመደጋገም እንደገለጽነው ህወሓት/ኢሕአዴግ ገና ከጥንስሱ ኢትዮጵያን ለማዳከምና ታሪኳን ለማጠልሸት አነጣጥሮ የመጣው አማራውን መፍጀትና ማዳከም፣ የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን ማድቀቅ እና የምዬ ምኒልክን ታሪክ ማጠልሸት ጋር ተጣምሮ የኢትዮጵያዊነት ክቡር መለያችንን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቃችንን ጨርቅ ከማለት አልፎ በመርገጥና በማቃጠል በኅብረተሰባችንና በትውልዱ ላይ ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ከቶም እንዳይኖር መጣር ነበር። ይህ ውጥን ያስከተለው ውጤት ቀላል ባይባልም ኢትዮጵያዊነት ግና ሕይወት ነውና፣ ኢትዮጵያዊነት ፍቅር ነውና፣ ኢትዮጵያዊነት አብሮነት ነውና አልተሳካምም፤ አይሳካምም።

ምንም ይባል ምን ወያኔ/ህወሓት/ኢሕአዴግ ለ27 ዓመታት ከተከመረባት ኢትዮጵያ ጫንቃ ላይ ተሸቀንጥሮ መፍረጥ ትልቅ ድል ነው። በምን ሁኔታ ወያኔ/ህወሓት ከሀገራችን ተወግዶ የሰላም አየር እንተነፍሳለን፣ መብታችንን እንጎናጸፋለን ብለን የጓጓንለት ሥርዓት ደስታውንና ጭፈራውን ሊቀበል ባይፈልግም ወያኔ/ህወሓት ዳግም እንዳያንሰራራ ኢትዮጵያን የሚል ሊተባበር እንደሚገባው ልንጠቁም እንወዳለን። የዶር ዐቢይ አገዛዝ አልተመቸንምና ለዚህ ነቀርሳ የወንበዴ መንግስት ወይም የመንግሥት ወንበዴ ለነበረ ቡድን ከሥልጣን መሽቀንጠር አይደለም ተቀብሮ ድራሹ እስኪጠፋ ካልተባበርን ያን ጊዜ ሀገር ብትበታተን፣ ሕዝባችን ቢጨፈጨፍ መጸጸቱ አዋጭ አይደለም። በዚህ ጉዳይ የትግራይን ሕዝብ እና ወያኔ/ህወሓት ነጥለን ማየት የኖርብናል። የትግራይ ሕጻናትና አዛውንት እንዲሁም ወጣቶች በወያኔ አልሞት ባይ ተጋዳይ ርዝራዦች የሽብር ጥቃት ላይ ተሰለፉ ብሎ የትግራይን ኅብረተሰብ ለማግለል መጣር ኢትዮጵያን የመበታተኑ አካል ይሳካላቸው ዘንድ ህልመኞቹ ወጥመድ መግባትን ያስከትላልና ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።

ከእንግዲህ ወያኔ/ህወሓት በምንም መልኩ ለዳግም ሥልጣን አይደለም ትግራይ ሊመሽግ አይገባውም። አፈሩን እባብ ያርግለትና የወያኔ/ህወሓት ብቸኛ ቦታ መቃብር መሆን ይኖርበታል። በጫካ ዘመናቸው 17 ዓመት፣ በሥልጣን ዘመናቸው 27 ዓመት በሕዝብ ልጆችና በሀገር ለተጫወቱት ምድሪቷ ከተቀበለቻቸው መቃብርም ሲበዛባቸው ነው። የወያኔ ርዝራዦች ከእንግዲህ ዳግም ሥልጣን ይዞ የማተራመስ ህልማቸው እንዳበቃ ቢረዱትም በቻሉት አቅም በተለያየ አቅጣጫ ከሽብር ተግባራቸው ወደኋላ እንደማይሉ እያሳዩ ነው። ለእነሱ የሰው ልጅ እልቂትና የሀገር ድቀት ግባቸው፣ ደስታቸው ነውና ኢትዮጵያችን ካልን ዘንዳ ወያኔ/ህወሓት እንዳያንሰራራ አድርገን ለመቅበር ሁሉም ጉድጓድ ቆፋሪ መሆን ይኖርበታል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ዶር ዐቢይ አሕመድ አገዛዝ ወያኔ/ህወሓት ዱቄት አደረኳቸው ብሎ ለሕዝብ ያልነበረ ተስፋ በተደጋጋሚ ከመስጠት አልፎ እዛው በተጀመረው ጦርነት በነበር ማስቀረት ነበረበት። አልሆነም። ትልቅ ስህተት። ዛሬ በሌሎች አካባቢዎች ለሌላ እልቂት ባልተዳረግን ነበር። ዛሬ እየተሰባሰበ ያለውን "ሕዝባዊ የክተት ጥሪ" ቀደም ሲል በኢትዮጵያችን እትም ቅጽ 3 ቁጥር 8 ሰኔ 27 ቀን 2011 ዓ.ም. (July 04, 2019) እንዲህ ስንል ገልጸን ነበር።

***". . . ኢትዮጵያ ችግር ላይ ብቻ ሳይሆን የእርስ በእርስ ጦርነት ሲጋት ላይ ናት። ሁሉም ነገ ምን ይከሰት ይሆን? እያሉ አምላካቸውን መማጸን ይዘዋል። በመንግሥት በኩል ያለው አመኔታ እየተመናመነ የመጣበት ሁኔታ ያለምክንያት አይደለም። የሚወራውና ምድር ላይ ያለው እጅግ የተራራቁ ናቸውና። <u>ጠ/ሚር ዶር ዐቢይ አሕመድ ኢትዮጵያን ከመበታተን ለማዳን በቅድሚያ ያለውን የዘረኝነት ችግር ለሕዝብ ይፋ አድርገው ሀገራችን ያለችበትን አደገኛ ሁኔታ በማሳወቅ ሕዝባዊ ጥሪ ማድረግ ይገባቸዋል። ሀገሩን፣ ሰንደቅ ዓላማውንና ሕዝቡን ወዳድ ኃይል ከጎናቸው ይሰለፍ ዘንድ ክተት! ማለት የሚገባቸው ወቅት ላይ እንደሆኑ ልንጠቁም እንወዳለን።</u> "አደባባሰው ቢያርሱ . . ." እንዳይሆን ችግሩን ለሀገሩና ለሰንደቅ ዓላማው ግምባሩን ከማያጥፈው ሕዝባችን ጋር ለመመከት በግልጽ መጋፈጥ ያለባቸው ወቅት መሆኑን እናሳስባለን። ይህ ካልሆነ አሁንም ዙሮ ዙሮ ኢትዮጵያ አትፈርስም! ግና አስደንጋጭ እልቂት ባንፈልገውም ፈላጊዎች ታጥቀዋልና፣ ባንመኘውም የተመኙ አሉና፣ ኢትዮጵያችን ስንል "ተረት ተረት" ባዮች ከበውናልና እግዚዮ! ከማለት ሌላ አማራጭ የለም።***

***'. . . ጠ/ሚር ዐቢይ አሕመድ አሁንም እውን ኢትዮጵያን ከመበታተንና ከእርስ በርስ ግጭት ለማዳን ቁርጠኛ አቋም ካላቸው የዘር ድርጅቶችንና ሕዝቡን ለይተው ማየት የኖርባቸዋል። ከጎናቸው ማሰለፍ የሚገባቸው ሁሉንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ኦሮሞ፣ አማራ፣ ትግሬ፣ አፋር፣ ቤኒ ሻንጉል፣***

***ጋምቤላ፣ ወላይታ፣ ሲዳማ፣ ጉራጌ፣ ሐደሬ፣ ደቡቡ፣ ምሥራቁ ሁሉም ሕዝባችን ሀገሩን ወዳድ፣ ሰንደቅ ዓላማውን አክባሪ ነውና ይህንን ዕድል ሊጠቀሙበት ይገባል ሰንል የማያቋርጥ ድምጻችንን እናስነብባለን።”*** የጥቅሱ መጨረሻ

የጠቅላይ ሚኒስትር አገዛዝ ጆሮ ላይሰጠው የፈለገውን መልዕክታችን ከሁለት ዓመት በኋላ ምላሹ በአማራው ተጋድሎ ውጤትና በሕዝባችን ሀገር ወዳድነት ሊተገበር ሕዝብ እራሱ “ክተት” ብሏል።

የዶክተር ዐቢይ አገዛዝ ስህተት ሰርቷልና ተቃውሞአችንን በማጠናከር ወያኔ/ህወሓት እንዲያንሰራራ ዕድል መስጠት እንደማይገባ አበክረን ለመግለጽ እንወዳለን። ወያኔ/ህወሓት ሀገር ላይ ከመጣ መቅሰፍት ለይተን ማየት የሌለብን የወንበዴ ቡድን ነው። መደጋገም አይሁንብንና 27 ዓመት የሀገርና ሕዝብን ንብረት ከመዝረፍ አልፎ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜታችንን በመቅበር ሀገር ተተኪ ትውልድ እንዳይኖራት የቻለውን ያህል የዘረኝነት መርዙን ቢረጭም በአሁኑ ወቅት እየታየ ያለው ሀገርን ለመከላከል መሰባሰብ ምስክር ነው። የትግራይ ሕዝብን ሳይሆን ወያኔ/ህወሓትን ከወልቃይት ጠገሌ ከማባረር ጀምሮ ድባቅ በመምታቱ ወደድንም ጠላን፣ ተቀበልነውም አልተቀበልነው አማራው ከፍተኛውን ሀገራዊ ድርሻ ተወጥቷል፤ እየተወጣም ይገኛል። **በበደኖና አርባ ጉጉ የጀመረውን የ27 ዓመቱን የአማራው እልቂት ትተን የሦስት ዓመቱን ብንመለከት እየዬ ከማሰኘት አልፎ ያደነዘዘ፣ የሰው ልጅ ከሚችለው በላይ ያልታሰበ፣ ያልተጠበቀ ግፍ ደርሶበታል። ይህ ዘግናኝ ፍጅት በወያኔ/ህወሓት አገዛዝ ዘመን ቢሆን ከወያኔ እንቁላል እርግብ አንጠብቅምና አያስደንቅም ነበር፤ ግና ለኢትዮጵያ መሪ መጣላት በማለት እናቶች በእልልታ፣ አባቶች በጭብጨባ፣ ወጣቶች በጭፈራ፣ ሕጻናት በፈገግታ በፈነደቁለት በዶር ዐቢይ አገዛዝ መሆኑ ብዙዎችን ቅስም ቢሰብርም አሁንም ለሀገር ሲባል፣ ሕዝብ ለጦርነት ክተት ሲል መንግሥት ይህንን ዕድል ትምህርት ወስዶ ሊጠቀምበት ይገባል።**

አማራው ብቻውን ህልውናውን ከማስጠበቅ አልፎ ለሀገሩና ለሰንደቅ ዓላማው እንደሚሰዋ አሳይቷል፣ ይቀጥላልም። የወያኔ/ህወሓት የዘር/ቋንቋ ከፋፍለህ ግዛው የጥቃቱ ሰለባ ቢያደርገውም ዛሬ ባለድል መሆኑን የሚያሳየው አማራውን ማገዝ ማለት ሀገርን መታደግ መሆኑን የተረዱ ሁሉ በወያኔ የዘርና ቋንቋ ክልል ባናምንበትም የየክልላቸውን ሠራዊት እና ሕዝብ ክተት እያሉ ነው። የአማራው የትግል ውጤት ሶማሌ፣ አፋር፣ ኦሮሞ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ፣ ጋምቤላ፣ አዲስ አበቤ፣ ሐረሬ ወዘተ. ብሔራዊ ክብራችን ሰንደቅ ዓላማ እያውለበለበ ክተት ሲል ሕዝባችን በየአካባቢው የአቅሙን ሲረባረብ መመልከት ያለብን ምን ያህል ወያኔ/ህወሓት ዳግም ማንሰራራት ለሀገር ጉዳት መሆኑን ሕዝብ ሲመለከት ስህተት ቤታቸው የሆነ ተማርን ያሉ ምሁሮቻችን፣ አወቅን ያሉ ፖለቲከኞቻችን ዳግም ስህተት እንዳይሰሩ ልንጠቁም እንወዳለን።

ትላንት በተሠራ ስህተት የጠ/ሚር ዐቢይን አገዛዝ ለማሽመድመድ የባዕዳን ሀገሮችን ፍላጎት ለማሟላት ድምጽን ማሰማት አግባብ አይደለም። ህወሓት/ወያኔ እንዲያንሰራራ ህልመኞች፣ የዘር ፖለቲካው ጡዘት “ተጠቃሚዎች” እና “እኛም ሀገር እንሁን” ባይ ከንቱዎች ናቸው። **ከቶም ሊያንሰራራ የማይገባው ህወሓት እንደ ደርግ ኢሠፓ ከታሪክ አተላ መደባለቅ ይገባዋልና ሀገር ፈራርሳ መጠገኑ ከባድ መስዋዕትነት ይጠይቃልና ወያኔን ቀብሮ የዶር ዐቢይ አገዛዝን መታገሉ ይመረጣል።**

በ6ኛው ዙር ምርጫ አሸናፊው ከዶር ዐቢይ ፓርቲና አገዛዙ ጋር የወያኔ/ህወሓት ሠነድ ሕገ መንግሥት መሻርና ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረገ አከላለል መወገድን ጨምሮ በሀገሪቷ ላይ የተከሰተው የኑሮ ማሻቀብ እጅግ በርካታ ትግሎች የሚያስፈልጉት ናቸው። በተጠያቂነትም ከተመጣ በወያኔ አገዛዝ ዘመን ሕይወታቸው በከንቱ የተቀጠፈውን ጨምሮ በእስር፣ በስደት፣ በአካል ጉዳት፣ ከንብረታቸውና ቀዬያቸው በመፈናቀል መከራና ስቃይ ያዩ ወገኖች ሁሉ የፍትህ ያለ እንደሚሉ ሁሉ

በዶር ዐቢይ አገዛዝም ለደረሰው ፍጅትና የአማራው እልቂት ጊዜ እንደሚጠይቅ ልንጠቁም እንወዳለን። ኢትዮጵያችንን የሕዝቧና የልጆቿ የማድረግ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለውጥ ገና ብዙ ፈተና ያለበት መስዋዕትነት ጠያቂ መሆኑን በመረዳት ለዚህ ትግል ግና የወያኔ/ህወሓት ተፈላጊነት ዜሮና ባዶ መሆን ይኖርበታል። ኢትዮጵያችን ላይ ለአለፉት 44 ዓመታት ያሳረፈው ስቃይ ከበቂ በላይ ነውና በወያኔ መቃብር ላይ ቀጣይ ትግላችንን ማድረግ ይመረጣል። ጭፍን ተቃዋሚ በመሆን ሀገር ላለመጉዳት ቆም ብለን እናስብ።

ታሪክን መለስ ብለን ስንቃኝ የዐድዋ ድል በምኒልክ የክተት ዘመቻ ሕዝቡ ከአራቱም አቅጣጫ ተሰባስቦ በአጭር ጊዜ ታሪካዊ ድል ሊያስመዘግብ ችሏል። የአምስቱ ዓመት ወረራም አርበኞቻችን በጫካውና በዱሩ ተሠማርተው ጠላትን መግቢያ መውጫ በማሳጣት ተዝናንቶ ሊንሰራፋ ያኮበኮበውን ወራሪ በአምስት ዓመት ውስጥ ድባቅ መተው የሀገርን ነጻነት አስረክበዋል። በደርግ ዘመን በሶማሌ ወረራ ወቅት ሕዝቡ የመንግሥትን ጥሪ ተቀብሎ ዳር እስከዳር በመንቀሳቀስ በአጭር ጊዜ ለድል በቅቷል። በጊዜው ደርግ ላይ ከሚካሄደው ትግል አንጻር ወረራውን ከደርግ ጎን ተሰልፎ በጋራ መመከት ሲገባ በጭፍን ተቃውሞ ብቻ የተሠራው ስህተት እንዳይደገም ማስገንዘብ ያስፈልጋል።

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በየክልሉ ወያኔን ለማጥፋት ጦርነቱን ሲደግፉ የወያኔን መርዝ ያውቁታልና ከጭንቅላቱ ካልተቀጠቀጠ ጊዜ እየጠበቀ እንዳያንሰራራ ከመገንዘብ በመሆኑ እምቢልታ ነፊውን፣ ነጋሪት ጎሳሚውን እናድምጥ። የዶር ዐቢይ አገዛዝ እጅግ ሥር ነቀል ጥያቄዎች ከፊቱ ተደቅነው ይጠብቁታል። ያለምንም ማመንታት ሊመልሳቸው ካልቻለ ወያኔ/ህወሓት ላይ የዘመተው ዱላ በቀጣይነት ዘረኝነት ላይ እንደሚዘምት አንጠራጠር። የዘርና ቋንቋ አከላለልና የወያኔ ሕገ መንግሥት ጊዜው ያለፈበት፣ የሰለቸ በመሆኑ ማብቃት አለበት ሲባል ኢትዮጵያ አንድነቷ ይጠንክር፣ ዘላለማዊነቷ መሠረት ይኑረው ማለት ነው። ዘረኝነትን ይዞ ሀገር መገንባት ሆነ እድገት ማስመዝገብ ከወሬ አይዘልም።

በዚህ ሕዝባዊ የክተት መሰባሰብ የሚደረገው ድጋፍ የገንዘብ፣ የቁሳቁስ፣ የምግብ ወዘተ ሆነ ጦርነቱን አቅጣጫ አሲዞ ከግብ ለማድረስ ሕዝቡን የወከለ "ሕዝባዊ የክተት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ" መዋቀር እንደሚያስፈልግ ልንጠቁም እንወዳለን። ወያኔ/ህወሓትን ለማጥፋት የሚካሄደው ፍልሚያው ያልተንዛዛና በአጭር ጊዜ ለአንዴም ለመጨረሻውም እንዳያንሰራራ አድርጎ የመቅበር ዘመቻው የተቀናጀ አመራርና ሎጂስቲክ እና ምግብ፣ ውሃ የመሳሰሉት አቅርቦት፣ የኋላ ደጀን አስፈላጊነቱን ተገንዝቦ የተሳካ አመራር ሰጪ ከየክልሉ ከተውጣጣው ጦር የተወከሉ ያሉበት "ሕዝባዊ የክተት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ" ወሳኝ መሆኑን እየጠቆምን መንግሥትም ይህን ግብረ ኃይል በመርዳትና በማገዝ የድርሻውን መወጣት ይኖርበታል እንላለን።

የጦርነት በጎ ጎን ባይኖረውም ሀገር እንዳትፈርስ መፍረስ ያለባቸው መሳሪያ መጨበጥን ግድ ያስብላሉ። እየተጨፈጨፈ ያለው አማራ ህልውናው የተቆራኘው ከሀገሩ ኢትዮጵያ ነውና "ሁሉም አማራ ለአንድ ኢትዮጵያ" ፉከራውን አድምቆ ወያኔ/ህወሓት ድባቅ መምታት ብቻ ሳይሆን ዘርና/ቋንቋን ተገን ያደረገ አጥር ተንዶ፣ ኢትዮጵያዊነት ከፍ ብሎ፣ ሁሉም ዘር ለኢትዮጵያ፣ ሁሉም ቋንቋ የኢትዮጵያ፣ ሁሉም ባህል ተወራራሽ፣ ሁሉም ሃይማኖት የግል፣ የሆነባት ሀገር በሕዝብ የበላይነት መሠረቱን ያገኝ፣ ይይዝ ዘንድ ትልቁ ዓላማችን/ሥዕላችን ሀገራችን ትሁን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!
ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይጠብቅ!!!
አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ
ሐምሌ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. (July 28, 2021)